# ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ።

(ክለሳ.1.20020507)

___________________ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ በዖዝያንና ፡ በኢዮአታም ፡ በአካዝና ፡ በሕዝቅያስም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በዮአስ ፡
ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ዘመን ፡ ወደብኤሪ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሆሴዕ ፡ የመጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ መዠመሪያ ፡ በሆሴዕ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሆሴዕን ፦ ምድሪቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ርቃ ፡ ታላቅ ፡ ግልሙትና ፡ ታደርጋለችና ፡ ኺድ ፤ ጋለሞታን ፡ ሴትና ፡ የግልሙትናን ፡ ልጆች ፡ ለአንተ ፡ ውሰድ ፡
አለው ።

3 ፤ ርሱም ፡ ኼዶ ፡ የዴቤላይምን ፡ ልጅ ፡ ጎሜርን ፡ አገባ ፤ ርሷም ፡ ፀነሰች ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደችለት ።

4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ከጥቂት ፡ ዘመን ፡ በዃላ ፡ የኢይዝራኤልን ፡ ደም ፡ በኢዩ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡
አበቀላለኹና ፥ ከእስራኤልም ፡ ቤት ፡ መንግሥትን ፡ አሽራለኹና ፡ ስሙን ፡ ኢይዝራኤል ፡ ብለኽ ፡ ጥራው ፤

5 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በኢይዝራኤል ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ የእስራኤልን ፡ ቀስት ፡ እሰብራለኹ ፡ አለው ።

6 ፤ ደግሞ ፡ ፀነሰች ፡ ሴት ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ። እግዚአብሔርም ፦ ይቅር ፡ እላቸው ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አልምርምና ፡ ስሟን ፡ ሎሩሃማ ፡ ብለኽ ፡ ጥራት ፤

7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ እምራለኹ ፤ በአምላካቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አድናቸዋለኹ ፡ እንጂ ፡ በቀስት ፡
ወይም ፡ በሰይፍ ፡ ወይም ፡ በሰልፍ ፡ ወይም ፡ በፈረሶች ፡ ወይም ፡ በፈረሰኛዎች ፡ አላድናቸውም ፡ አለው ።

8 ፤ ሎሩሃማም ፡ ጡት ፡ ባስጣለች ፡ ጊዜ ፥ ደግሞ ፡ ፀነሰች ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ።

9 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ሕዝቤ ፡ አይደላችኹምና ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ አልኾናችኹምና ፡ ስሙን ፡ ሎዓሚ ፡ ብለኽ ፡
ጥራው ፡ አለው ።

___________________ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ቍጥር ፡ እንደማይሰፈርና ፡ እንደማይቈጠር ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይኾናል ፤ እንዲህም ፡
ይኾናል ፤ እናንተ ፡ ሕዝቤ ፡ አይደላችኹም ፡ ተብሎ ፡ በተነገረበት ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ የሕያው ፡ አምላክ ፡ ልጆች ፡ ይባላሉ ።

2 ፤ የይሁዳ ፡ ልጆችና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ይሰበሰባሉ ፥ ለእነርሱም ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡
ይሾማሉ ፥ ከምድሪቱም ፡ ይወጣሉ ፤ የኢይዝራኤል ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ይኾናልና ።

3 ፤ ወንድሞቻችኹን ፦ ዓሚ ፥ እኅቶቻችኹንም ፦ ሩሃማ ፡ በሏቸው ።

4 ፤ እናታችኹ ፡ ሚስቴ ፡ አይደለችምና ፥ እኔም ፡ ባሏ ፡ አይደለኹምና ፡ ተሟገቱ ፤ ከእናታችኹ ፡ ጋራ ፡
ተሟገቱ ። ግልሙትናዋን ፡ ከፊቷ ፥ ምንዝርናዋንም ፡ ከጡቶቿ ፡ መካከል ፡ ታስወግድ ፤

5 ፤ ዕራቍቷን ፡ እንዳልገፋት ፥ እንደተወለደችበትም ፡ ቀን ፡ እንዳላደርጋት ፥ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳና ፡ እንደ ፡ ደረቅ ፡
ምድር ፡ እንዳላደርጋት ፥ በጥማትም ፡ እንዳልገድላት ፤

6 ፤ የግልሙትናዋ ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ፥ ልጆቿን ፡ አልምርም ።

7 ፤ እናታቸው ፡ አመንዝራለች ፤ የፀነሰቻቸውም ፦ እንጀራዬንና ፡ ውሃዬን ፥ ጥጤንና ፡ የተልባ ፡ እግሬን ፥ ዘይቴንና ፡
መጠጤን ፡ ከሚሰጡኝ ፡ ከውሽማዎቼ ፡ በዃላ ፡ እኼዳለኹ ፡ ብላ ፡ አስነወረቻቸው ።

8 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ መንገድሽን ፡ በሾኽ ፡ እዘጋለኹ ፥ መንገዷንም ፡ እንዳታገኝ ፡ ቅጥርን ፡ እቀጥርባታለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

9 ፤ ውሽማዎቿንም ፡ ትከተላለች ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትደርስባቸውም ፤ ትፈልጋቸውማለች ፥ ነገር ፡
ግን ፥ አታገኛቸውም ፤ ርሷም ፦ ከዛሬ ፡ ይልቅ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይሻለኛ ፡ ነበርና ፥ ተመልሼ ፡ ወደቀደመው ፡ ባሌ ፡
እኼዳለኹ ፡ ትላለች ።

10 ፤ ርሷም ፡ እኽልንና ፡ ወይንን ፡ ጠጅ ፡ ዘይትንም ፡ የሰጠ኿ት ፥ ለበዓልም ፡ የተሠራውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ያበዛኹላት ፡
እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ አላወቀችም ።

11 ፤ ስለዚህ ፥ እኽሌን ፡ በጊዜዋ ፥ ወይን ፡ ጠጄንም ፡ በወረቷ ፡ እወስዳለኹ ፥ ዕራቍትነቷንም ፡ እንዳትሸፍን ፡ ጥጤንና ፡
የተልባ ፡ እግሬን ፡ እገፋታለኹ ።

12 ፤ አኹንም ፡ ውሽማዎቿ ፡ እያዩ ፡ ነውሯን ፡ እገልጣለኹ ፤ ከእጄም ፡ ማንም ፡ አያድናትም ።

13 ፤ ደስታዋንም ፡ ኹሉ ፥ በዓላቷንም ፥ መባቻዎቿንም ፥ ሰንበቶቿንም ፥ የተቀደሱትንም ፡ ጉባኤዎችን ፡ ኹሉ ፡
አስቀራለኹ ።

14 ፤ ርሷም ፦ ውሽማዎቼ ፡ የሰጡኝ ፡ ዋጋዬ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ያለችውን ፡ ወይኗንና ፡ በለሷን ፡ አጠፋለኹ ፤ ዱርም ፡
አደርገዋለኹ ፥ የምድረ ፡ በዳም ፡ አራዊት ፡ ይበሉታል ።

15 ፤ እኔን ፡ ረስታ ፡ ውሽማዎቿን ፡ እየተከተለች ፥ በጒትቾቿና ፡ በጌጧም ፡ እያጌጠች ፡ ለበዓሊም ፡ ያጠነችበትን ፡
ወራት ፡ እበቀልባታለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

16 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ አባብላታለኹ ፥ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ አመጣታለኹ ፥ ለልቧም ፡ እናገራለኹ ።

17 ፤ ከዚያም ፡ የወይን ፡ ቦታዋን ፥ የተስፋ ፡ በርም ፡ እንዲኾንላት ፡ የዐኮርን ፡ ሸለቆ ፡ እሰጣታለኹ ፤ በዚያም ፡ ከግብጽ ፡
ምድር ፡ እንደ ፡ ወጣችበት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ሕፃንነቷ ፡ ወራት ፡ ትዘምራለች ።

18 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ባሌ ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪኛለሽ ፡ እንጂ ፡ ዳግመኛ ፡ በኣሌ ፡ ብለሽ ፡ አትጠሪኝም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

19 ፤ የበዓሊምን ፡ ስም ፡ ከአፏ ፡ አስወግደዋለኹና ፥ በስማቸውም ፡ እንግዲህ ፡ አይታሰቡምና ።

20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከምድር ፡ አራዊትና ፡ ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ከመሬትም ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
አደርግላቸዋለኹ ፤ ቀስትንና ፡ ሰይፍን ፡ ሰልፍንም ፡ ከምድሩ ፡ እሰብራለኹ ፥ ተከልለውም ፡ እንዲኖሩ ፡ አስተኛቸዋለኹ ።

21 ፤ ለዘለዓለምም ፡ ለእኔ ፡ እንድትኾኚ ፡ ዐጭሻለኹ ፤ በጽድቅና ፡ በፍርድ ፡ በምሕረትና ፡ በርኅራኄ ፡ ዐጭሻለኹ ።

22 ፤ ለኔም ፡ እንድትኾኚ ፡ በመታመን ፡ ዐጭሻለኹ ፤ አንቺም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታውቂያለሽ ።

23 ፤ በዚያንም ፡ ቀን ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ለሰማይ ፡ እመልሳለኹ ፥ ሰማይም ፡ ለምድር ፡ ይመልሳል ፤

24 ፤ ምድርም ፡ ለእኽልና ፡ ለወይን ፡ ጠጅ ፡ ለዘይትም ፡ ትመልሳለች ፤ እነርሱም ፡ ለኢይዝራኤል ፡ ይመልሳሉ ።

25 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ለእኔ ፡ እዘራታለኹ ፤ ምሕረትም ፡ የሌላትን ፡ እምራለኹ ፥ ሕዝቤም ፡ ያልኾነውን ፦ አንተ ፡
ሕዝቤ ፡ ነኽ ፡ እለዋለኹ ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ፡ ይለኛል ።

__________________ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ እግዚአብሐርም ፦ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ቢመለሱና ፡ የዘቢብ ፡ ጥፍጥፍን ፡ ቢወዱ ፡
እንኳ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንደሚወዳቸው ፡ አንተም ፡ ውሽማዋን ፡ የምትወደውን ፡ አመንዝራዪትን ፡ ሴት ፡ ውደድ ፡
አለኝ ።

2 ፤ እኔም ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ብርና ፡ ባንድ ፡ ቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ተኩል ፡ ገብስ ፡ ገዛኋት ።

3 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ተቀመጪ ፥ አታመንዝሪም ፥ ለሌላ ፡ ሰውም ፡ አትኹኚ ፤ እኔም ፡ እንዲሁ ፡
እኾንልሻለኹ ፡ አልኋት ።

4 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ያለንጉሥና ፡ ያለአለቃ ፥ ያለመሥዋዕትና ፡ ያለዐምድ ፥ ያለኤፉድና ፡ ያለተራፊም ፡ ብዙ ፡
ወራት ፡ ይቀመጣሉና ፤



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተመልሰው ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሣቸውን ፡ ዳዊትን ፡
ይፈልጋሉ ፤ በኋለኛውም ፡ ዘመን ፡ ፈርተው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ወደ ፡ በረከቱ ፡ ይመጣሉ ።

## ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እውነትና ፡ ምሕረት ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ማወቅ ፡ በምድር ፡ ስለሌለ ፡
እግዚአብሔር ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ ከሚኖሩ ፡ ጋራ ፡ ክርክር ፡ አለውና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

2 ፤ ርግማንና ፡ ሐሰት ፡ ግዳይና ፡ ስርቆት ፡ ምንዝርናም ፡ ወጥተዋል ፤ ደምም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ደርሷል ።

3 ፤ ስለዚህ ፥ ምድሪቱ ፡ ታለቅሳለች ፥ በርሷም ፡ የሚቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ ከምድር ፡ አራዊትና ፡ ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ጋራ ፡
ይደክማሉ ፤ የባሕሩም ፡ ዓሣዎች ፡ ያልቃሉ ።

4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሕዝብኽ ፡ ከካህን ፡ ጋራ ፡ እንደሚከራከሩ ፡ ናቸውና ፥ ማንም ፡ አይከራከር ፥ ማንም ፡ አይዝለፍ ።

5 ፤ በቀንም ፡ ትሰናከላለኽ ፥ ነቢዩም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በሌሊት ፡ ይሰናከላል ፤ እናትኽንም ፡ አጠፋታለኹ ።

6 ፤ ሕዝቤ ፡ ዕውቀት ፡ ከማጣቱ ፡ የተነሣ ፡ ጠፍቷል ፤ አንተም ፡ ዕውቀትን ፡ ጠልተኻልና ፥ እኔ ፡ ካህን ፡ እንዳትኾነኝ ፡
እጠላኻለኹ ፤ የአምላክኽንም ፡ ሕግ ፡ ረስተኻልና ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ልጆችኽን ፡ እረሳለኹ ።

7 ፤ እንደ ፡ ብዛታቸው ፡ መጠን ፡ ኀጢአት ፡ ሠሩብኝ ፤ እኔም ፡ ክብራቸውን ፡ ወደ ፡ ነውር ፡ እለውጣለኹ ።

8 ፤ የሕዝቤም ፡ ኀጢአት ፡ መብል ፡ ኾኖላቸዋል ፥ ልባቸውንም ፡ ወደ ፡ በደላቸው ፡ አድርገዋል ።

9 ፤ እንደ ፡ ሕዝቡም ፡ እንዲሁ ፡ ካህኑ ፡ ይኾናል ፤ በመንገዳቸውም ፡ እበቀላቸዋለኹ ፥ ሥራቸውንም ፡
እመልስባቸዋለኹ ።

10 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ መጠበቅ ፡ ትተዋልና ፥ ሲበሉ ፡ አይጠግቡም ፥ ሲያመነዝሩም ፡ አይበዙም ።

11 ፤ ግልሙትናና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ስካርም ፡ አእምሮን ፡ ያጠፋል ።

12 ፤ የግልሙትና ፡ መንፈስ ፡ ሕዝቤን ፡ አስቷቸዋልና ፥ እነርሱም ፡ ከአምላካቸው ፡ ርቀው ፡
አመንዝረዋልና ፥ በትራቸውን ፡ ይጠይቃሉ ፥ ዘንጋቸውም ፡ ይመልስላቸዋል ።

13 ፤ በተራራዎችም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይሠዋሉ ፤ ጥላውም ፡ መልካም ፡ ነውና ፥ ከኮምበልና ፡ ከልብን ፣ ከአሆማም ፡ ዛፍ ፡
በታች ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያጥናሉ ፤ ስለዚህ ፥ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹ ፡ ይገለሙታሉ ፥ ሙሽሮቻችኹም ፡ ያመነዝራሉ ።

14 ፤ ወንዶችም ፡ ደግሞ ፡ ከጋለሞታዎች ፡ ጋራ ፡ ይጫወታሉና ፥ ከጋለሞታዎችም ፡ ጋራ ፡ ይሠዋሉና ፡ ሴቶች ፡
ልጆቻችኹ ፡ በገለሞቱ ፡ ጊዜ ፥ ሙሽሮቻችኹም ፡ ባመነዘሩ ፡ ጊዜ ፡ አልቀጣቸውም ፤ የማያስተውልም ፡ ሕዝብ ፡
ይገለበጣል ።

15 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ብታመነዝር ፡ ይሁዳ ፡ አይበድል ፤ እናንተም ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ አትግቡ ፥ ወደ ፡
ቤትአዌንም ፡ አትውጡ ፥ ወይም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ብላችኹ ፡ አትማሉ ።

16 ፤ እስራኤል ፡ እንደ ፡ እልከኛ ፡ ጊደር ፡ እንቢ ፡ ብሏል ፤ እግዚአብሔርስ ፡ በሰፊው ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ጠቦት ፡
ያሰማራዋልን ፧

17 ፤ ኤፍሬም ፡ ከጣዖታት ፡ ጋራ ፡ ተጋጠመ ፤ ተወው ።

18 ፤ ስካርን ፡ ፈጽመዋል ፥ ግልሙትናንም ፡ አብዝተዋል ፤ አለቃዎቿም ፡ ነውርን ፡ እጅግ ፡ ወደዱ ።

19 ፤ ነፋስ ፡ በክንፏ ፡ አስሯታል ፤ ከመሥዋዕታቸውም ፡ የተነሣ ፡ ያፍራሉ ።

## ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ ካህናት ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ስሙ ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ አድምጡ ፤ የንጉሥ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ልብ ፡



www.ethiopianorthodox.org

አድርጉ ፤ በምጽጳ ፡ ላይ ፡ ወጥመድ ፥ በታቦርም ፡ ላይ ፡ የተዘረጋ ፡ አሽክላ ፡ ኾናችኋልና ፥ ፍርድ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡
ነው ።

2 ፤ ዐመፀኛዎችም ፡ ዕርድ ፡ አብዝተዋል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እነዚያን ፡ ዅሉ ፡ እዘልፋለኹ ።

3 ፤ ኤፍሬምን ፡ ዐውቀዋለኹ ፥ እስራኤልም ፡ ከእኔ ፡ አልተሰወረም ፤ ኤፍሬም ፡ ሆይ ፥ ዛሬ ፡
አመንዝረኻል ፥ እስራኤልም ፡ ረክሷል ።

4 ፤ ወደ ፡ አምላካቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ሥራቸውን ፡ አላቀኑም ፤ የግልሙትና ፡ መንፈስ ፡ በውስጣቸው ፡
አለና ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አላወቁምና ።

5 ፤ የእስራኤልም ፡ ትዕቢት ፡ በፊቱ ፡ ይመሰክራል ፤ ስለዚህ ፥ እስራኤልና ፡ ኤፍሬም ፡ በኀጢአታቸው ፡
ይሰናከላሉ ፤ ይሁዳም ፡ ደግሞ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ይሰናከላል ።

6 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ለመሻት ፡ በጎቻቸውንና ፡ ላሞቻቸውን ፡ ነድተው ፡ ይኼዳሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ ከነርሱም ፡
ተመልሷልና ፥ አያገኙትም ።

7 ፤ ዲቃላዎችን ፡ ልጆች ፡ ወልደዋልና ፥ እግዚአብሔርን ፡ ወንጅለዋል ፤ አኹንም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ እነርሱንና ፡
ርስታቸውን ፡ ይበላቸዋል ።

8 ፤ በጊብዓ ፡ መለከትን ፥ በራማ ፡ እንቢልታን ፡ ንፉና ፦ ብንያም ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በኋላ ፥ እያላችኹ ፡ በቤትአዌን ፡
ላይ ፡ እሪ ፡ በሉ ።

9 ፤ ኤፍሬም ፡ በዘለፋ ፡ ቀን ፡ የፈረሰ ፡ ይኾናል ። በእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ዘንድ ፡ በርግጥ ፡ የሚኾነውን ፡ ነገር ፡
ገልጫለኹ ።

10 ፤ የይሁዳ ፡ አለቃዎች ፡ ድንበርን ፡ እንደሚነቅሉ ፡ ኾነዋል ፤ እኔም ፡ መዓቴን ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አፈስ̇ባቸዋለኹ ።

11 ፤ ኤፍሬም ፡ ከትእዛዝ ፡ በኋላ ፡ መኼድን ፡ ወዷ̇ልና ፥ የተገፋና ፡ በፍርድ ፡ የተጐዳ ፡ ኾኗል ።

12 ፤ እኔም ፡ ለኤፍሬም ፡ እንደ ፡ ብል ፥ ለይሁዳም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ነቀዝ ፡ ኾኛለኹ ።

13 ፤ ኤፍሬምም ፡ ደዌውን ፥ ይሁዳም ፡ ቍስሉን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ኤፍሬም ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ኼደ ፡ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡
ኢያሪም ፡ መልእክተኛን ፡ ላከ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ይፈውሳችኹ ፡ ዘንድ ፥ ከቍስላችኹም ፡ ያድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም ።

14 ፤ እኔም ፡ ለኤፍሬም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፥ ለይሁዳም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ደቦል ፡ እኾናለኹና ፤ እኔም ፡ ነጥቄ ፡
እኼዳለኹ ፡ እወስድማለኹ ፥ የሚያድንም ፡ አይገኝም ።

15 ፤ በደላቸውንም ፡ እስኪያውቁ ፡ ድረስ ፥ ፊቴንም ፡ እስኪሹ ፡ ድረስ ፡ ኼጄ ፡ ወደ ፡ ስፍራዬ ፡
እመለሳለኹ ፤ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ፊቴን ፡ ይፈልጋሉ ።

____________________ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 6 ።

1 ፤ ኑ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንመለስ ፤ ርሱ ፡ ሰብሮናልና ፥ ርሱም ፡ ይፈውሰናል ፤ ርሱ ፡ መቶ̇ናል ፥ ርሱም ፡
ይጠግነናል ።

2 ፤ ከኹለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ያድነናል ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ያስነሣናል ፥ በፊቱም ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለን ።

3 ፤ እንወቅ ፤ እናውቀውም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንከተል ፤ እንደ ፡ ወገግታም ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እናገኘዋለን ፤ እንደ ፡
ዝናብም ፡ ምድርንም ፡ እንደሚያጠጣ ፡ እንደ ፡ መጨረሻ ፡ ዝናብ ፡ ይመጣል ።

4 ፤ ምሕረታችኹ ፡ እንደ ፡ ማለዳ ፡ ደመና ፥ በማለዳም ፡ እንደሚያልፍ ፡ ጠል ፡ ነውና ፥ ኤፍሬም ፡ ሆይ ፥ ምን ፡
ላድርግልኽ ፤ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ላድርግልኽ ፤

5 ፤ ስለዚህ ፥ በነቢያት ፡ እጅ ፡ ቈረጥኋቸው ፥ በአፌም ፡ ቃል ፡ ገደልኋቸው ፤ ፍርዴም ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ይወጣል ።

6 ፤ ከመሥዋዕት ፡ ይልቅ ፡ ምሕረትን ፥ ከሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ ይልቅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማወቅ ፡ እወዳለኹና ።

7 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ ተላልፈዋል ፤ በዚያም ፡ ላይ ፡ ወንጅለውኛል ።

8 ፤ ገለዓድ ፡ ኀጢአትን ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ከተማ ፥ በደምም ፡ የተቀባ ፡ ነው ።

9 ፤ ለሰውም ፡ እንደሚያደቡ ፡ ወንበዴዎች ፥ እንዲሁ ፡ የካህናት ፡ ወገኖች ፡ በሴኬም ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡
ይገድላሉ ፤ ሴሰኝነትንም ፡ ያደርጋሉ ።

10 ፤ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ የሚያስፈራን ፡ ነገር ፡ አይቻለኹ ፤ በዚያ ፡ በኤፍሬም ፡ ውስጥ ፡ ግልሙትና ፡
ተገኘ ፥ እስራኤልም ፡ ረክሷል ።

11 ፤ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ የሕዝቤን ፡ ምርኮ ፡ በምመልስበት ፡ ጊዜ ፡ ለአንተ ፡ ደግሞ ፡ መከር ፡ ተወስኖልኻል ።

## ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ምዕራፍ ፡ 7 ።

1 ፤ በሐሰት ፡ አድርገዋልና ፥ ሌባም ፡ ገብቷልና ፥ በውጭም ፡ ወንበዴዎች ፡ ቀምተዋልና ፥ እስራኤልን ፡ እፈውስ ፡ ዘንድ ፡
በወደድኹ ፡ ጊዜ ፡ የኤፍሬም ፡ ኀጢአትና ፡ የሰማርያ ፡ ክፋት ፡ ተገለጠ ።

2 ፤ እኔም ፡ ክፋታቸውን ፡ ዅሉ ፡ እንዳሰብኹ ፡ በልባቸው ፡ አያስቡም ፡ አኹንም ፡ ሥራቸው ፡ ከባቸዋለች ፥ በፊቴም ፡
አለች ።

3 ፤ ንጉሡን ፡ በክፋታቸው ፥ አለቃዎቹንም ፡ በሐሰታቸው ፡ ደስ ፡ አሰኝተዋል ።

4 ፤ ዅሉም ፡ አመንዝራዎች ፡ ናቸው ፤ ጋጋሪ ፡ እንደሚያነድበት ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ ናቸው ፤ ዅሉ ፡ እስኪቦካ ፡ ድረስ ፡
እሳትን ፡ መቈስቈስና ፡ ርሾን ፡ መለወስ ፡ ይቈያል ።

5 ፤ በንጉሣችን ፡ ቀን ፡ አለቃዎች ፡ ከወይን ፡ ጠጅ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ታመሙ ፤ ርሱም ፡ ከዋዘኛዎች ፡ ጋራ ፡ እጁን ፡
ዘረጋ ።

6 ፤ እያደቡ ፡ ልባቸውን ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ አዘጋጅተዋል ፤ አበዛቸውም ፡ ሌሊቱን ፡ ዅሉ ፡ አንቀላፋ ፤ በጠባም ፡ ጊዜ ፡
እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ይነዳል ።

7 ፤ ዅሉም ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ ግለዋል ፥ ፈራጆቻቸውንም ፡ በሉ ፤ ነገሥታታቸውም ፡ ዅሉ ፡ ወደቁ ፤ ከነርሱም ፡ ወደ ፡
እኔ ፡ የሚጮኽ ፡ የለም ።

8 ፤ ኤፍሬም ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ተደባለቀ ፤ ኤፍሬም ፡ እንዳልተገላበጠ ፡ ቂጣ ፡ ነው ።

9 ፤ እንግዳዎች ፡ ጕልበቱን ፡ በሉት ፥ ርሱም ፡ አላወቀም ፤ ሽበትም ፡ ወጣበት ፥ ርሱም ፡ አላወቀም ።

10 ፤ የእስራኤልም ፡ ትዕቢቱ ፡ በፊቱ ፡ መሰከረ ፤ ወደ ፡ አምላካቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡
አልተመለሱም ፥ በዚህም ፡ ዅሉ ፡ አልፈለጉትም ።

11 ፤ ኤፍሬምም ፡ አእምሮ ፡ እንደሌላት ፡ እንደ ፡ሰነፍ ፡ ርግብ ፡ ነው ፤ ግብጽን ፡ ጠሩ ፥ ወደ ፡ አሶርም ፡ ኼዱ ።

12 ፤ ሲኼዱ ፡ አሽክላዬን ፡ እዘረጋባቸዋለኹ ፤ እንደሰማይ ፡ ወፎች ፡ አወርዳቸዋለኹ ፤ መከራቸውን ፡ ሲሰሙ ፡
እገሥጻቸዋለኹ ።

13 ፤ ከእኔ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋልና ፥ ወዮላቸው! በእኔም ፡ ላይ ፡ ዐምፀዋልና ፥ ጥፋት ፡ ይምጣባቸው! እኔ ፡ ልታደጋቸው ፡
ወደድኹ ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ በሐሰት ፡ ተናገሩብኝ ።

14 ፤ በመኝታቸው ፡ ላይ ፡ ዅነው ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በልባቸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልጮኹም ፤ ስለ ፡ እኽልና ፡ ስለ ፡
ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይሰበሰቡ ፡ ነበር ፤ በእኔም ፡ ላይ ፡ ዐመፁ ።

15 ፤ እኔም ፡ ክንዳቸውን ፡ አስተማርኹና ፡ አጸናኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ መከሩብኝ ።

16 ፤ ወደ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ተመለሱ ፤ እንደ ፡ ተንኰለኛ ፡ ቀስት ፡ ኾኑ ፤ አለቃዎቻቸው ፡ ከምላሳቸው ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፡
በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፤ ይህ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ መሳለቂያ ፡ ይኾንባቸዋል ።

## ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 8 ።

1 ፤ መለከትን ፡ ወደ ፡ አፍኽ ፡ አቅርብ ፤ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ተላልፈዋልና ፥ በሕጌም ፡ ላይ ፡ ዐምፀዋልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ይመጣል ።

2 ፤ እነርሱም ፦ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እኛ ፡ እስራኤል ፡ ዐወቅንኽ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይጮኻሉ ።

3 ፤ እስራኤል ፡ ደግነትን ፡ ጥሏል ፤ ጠላትም ፡ ያሳድዱታል ።

4 ፤ ለራሳቸው ፡ ነገሥታትን ፡ አነገሡ ፥ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ፤ አለቃዎችንም ፡ አደረጉ ፥ እኔም ፡ አላወቅኹም ፤ ለጥፋታቸውም ፡ ከብራቸውና ፡ ከወርቃቸው ፤ ጣዖታትን ፡ ለራሳቸው ፡ አደረጉ ።

5 ፤ ሰማርያ ፡ ሆይ ፥ እንቦሳኽን ፤ ጥሏል ፤ ቍጣዬ ፡ በላያቸው ፡ ነዷል ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ንጹሕ ፡ ሊኾኑ ፡ አይችሉም ፨

6 ፤ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ሠራተኛ ፡ ሠራው ፥ ርሱም ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፤ የሰማርያም ፡ እንቦሳ ፡ ይቈራረጣል ።

7 ፤ ነፋስን ፡ ዘርተዋል ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስንም ፡ ያጭዳሉ ፤ አገዳ ፡ የለውም ፥ ከፍሬውም ፡ ዱቄት ፡ አይገኝም ፤ ቢገኝም ፡ እንግዳዎች ፡ ይበሉታል ።

8 ፤ እስራኤል ፡ ተውጧል ፥ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ረከሰ ፡ ዕቃ ፡ ኾኗል ።

9 ፤ ለብቻውም ፡ እንደሚቀመጥ ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አህያ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ወጥተዋል ፤ ኤፍሬምም ፡ ወዳጆቹን ፡ በእጅ ፡ መንሻ ፡ ገዛ ።

10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለአሕዛብ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ቢሰጡ ፡ እኔ ፡ አኹን ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፤ ከንጉሥና ፡ ከአለቃዎችም ፡ ሸክም ፡ የተነሣ ፡ ይደክማሉ ።

11 ፤ ኤፍሬም ፡ ኀጢአትን ፡ ለመሥራት ፡ መሠዊያ ፡ አብዝቷልና ፥ መሠዊያ ፡ ለኀጢአት ፡ ይኾንለታል ።

12 ፤ የሕጌን ፡ ብዛት ፡ ጽፌለታለኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ቈጥረውታል ።

13 ፤ መሥዋዕቴን ፡ ያቀርባሉ ፥ ሥጋንም ፡ ያርዳሉ ፥ ይበላሉም ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አይቀበላቸውም ፤ በደላቸውንም ፡ ያስባል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቀጣል ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመለሳሉ ።

14 ፤ እስራኤል ፡ ፈጣሪውን ፡ ረስቷል ፥ መስገጃዎችንም ፡ ሠርቷል ፤ ይሁዳም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ አብዝቷል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በከተማዎች ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰዳለኹ ፥ አዳራሾችንም ፡ ትበላለች ።

____________________ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 9 ።

1 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ከአምላክኽ ፡ ተለይተኽ ፡ አመንዝረኻልና ፥ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ደስ ፡ አይበልኽ ፥ ሐሤትንም ፡ አታድርግ ፤ በእኽሉ ፡ ዐውድማ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የግልሙትናን ፡ ዋጋ ፡ ወደኻል ።

2 ፤ ዐውድማውና ፡ መጥመቂያው ፡ አይመግባቸውም ፥ ጕሽ ፡ ጠጅም ፡ ይጐድልባታል ።

3 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አይቀመጡም ፤ ኤፍሬምም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመለሳል ፥ በአሶርም ፡ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ይበላሉ ።

4 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ የወይን ፡ ጠጅን ፡ ቍርባን ፡ አያፈሱም ፥ መሥዋዕታቸውም ፡ ደስ ፡ አያሠኘውም ፤ የሐዘንም ፡ እንጀራ ፡ ይኾንላቸዋል ፥ የሚበላውም ፡ ኹሉ ፡ ይረክሳል ፤ እንጀራቸውም ፡ ለሰውነታቸው ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አይገባም ።

5 ፤ በዓመት ፡ በዓል ፡ ቀንና ፡ በእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ታደርጋላችኹ ፨

6 ፤ እንሆ ፥ ከጥፋት ፡ ሸሽተው ፡ ኼዱ ፥ ግብጽም ፡ ትሰበስባቸዋለች ፥ ሜምፎስም ፡ ትቀብራቸዋለች ፤ ሳማም ፡ የብራቸውን ፡ ጌጥ ፡ ይወርሳል ፥ ሾኽም ፡ በድንኳኖቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ይበቅላል ።



www.ethiopianorthodox.org

7 ፤ የበቀል ፡ ወራት ፡ መጥቷል ፥ የፍዳም ፡ ወራት ፡ ደርሷል ፥ እስራኤልም ፡ ያውቃል ፤ ከኀጢአትኽና ፡ ከጠላትነትኽ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ነቢዩ ፡ ሰንፏል ፥ መንፈስም ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ አብዷል ።

8 ፤ ኤፍሬም ፡ ከአምላኬ ፡ ጋራ ፡ ተመልካች ፡ ነበረ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ነቢዩ ፡ በመንገዱ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የወፍ ፡ ወጥመድ ፡ ኾነ ፥ በአምላኩም ፡ ቤት ፡ ጠላትነት ፡ አለ ።

9 ፤ በጊብዓ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እጅግ ፡ ረከሱ ፤ ርሱም ፡ በደላቸውን ፡ ያስባል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይበቀላል ።

10 ፤ እስራኤልን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ወይን ፡ ኾኖ ፡ አገኘኹት ፤ አባቶቻችኹንም ፡ ከመዠመሪያዋ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ በለስ ፡ በኵራት ፡ ኾነው ፡ አየኋቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ብዔልፌጎር ፡ መጡ ፥ ለነውርም ፡ ተለዩ ፥ እንደ ፡ ወደዱትም ፡ ርኩስ ፡ ኾኑ ፥

11 ፤ የኤፍሬምም ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ በሮ ፡ ይጠፋል ፤ መውለድና ፡ መፅነስ ፡ ማርገዝም ፡ አይኾንላቸውም ።

12 ፤ ልጆቻቸውንም ፡ ቢያሳድጉ ፡ ሰው ፡ እንዳይቀርላቸው ፡ ልጅ ፡ አልባ ፡ አደርጋቸዋለኹ ፤ ከነርሱም ፡ በራቅኹ ፡ ጊዜ ፡ ወዮላቸው!

13 ፤ እኔ ፡ እንዳየኹ ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ለምርኮ ፡ ተሰጥተዋል ፤ ኤፍሬምም ፡ ልጆቹን ፡ ወደ ፡ ገዳዮች ፡ ያወጣል ።

14 ፤ አቤቱ ፥ ስጣቸው ፤ ምን ፡ ትሰጣቸዋለኽ ፧ የሚጨነግፍን ፡ ማሕፀን ፡ የደረቀውንም ፡ ጡት ፡ ስጣቸው ።

15 ፤ ክፋታቸው ፡ ኹሉ ፡ በገልገላ ፡ አለ ፤ በዚያ ፡ ጠልቻቸዋለኹ ፤ ስለሥራት ፡ ክፋት ፡ ከቤቴ ፡ አሳድዳቸዋለኹ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አልወዳቸውም ፤ አለቃዎቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ዐመፀኛዎች ፡ ናቸው ።

16 ፤ ኤፍሬም ፡ ተመታ ፥ ሥሩም ፡ ደረቀ ፥ ፍሬም ፡ አያፈራም ፤ ደግሞም ፡ ቢወልዱ ፡ የማሕፀናቸውን ፡ ፍሬ ፡ እገድላለኹ ።

17 ፤ አልሰሙትምና ፡ አምላኬ ፡ ይጥላቸዋል ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ተቅበዝባዦች ፡ ይኾናሉ ።

_______________ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _______________

ምዕራፍ ፡ 10 ።

1 ፤ እስራኤል ፡ ፍሬው ፡ የበዛለት ፡ የለመለመ ፡ ወይን ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ፍሬው ፡ ብዛት ፡ መሠዊያውን ፡ አብዝቷል ፤ እንደ ፡ ምድሩም ፡ ማማር ፡ መጠን ፡ ሐውልቶችን ፡ አያሳመሩ ፡ ሠርተዋል ።

2 ፤ ልባቸው ፡ ተከፈለ ፤ አኹንም ፡ በደላቸውን ፡ ይሸከማሉ ፤ ርሱ ፡ መሠዊያቸውን ፡ ያፈርሳል ፥ ሐውልቶቻቸውን ፡ ያጠፋል ።

3 ፤ አኹንም ፦ ንጉሥ ፡ የለንም ፥ እግዚአብሔርን ፡ አልፈራንምና ፤ ንጉሥስ ፡ ምን ፡ ያደርግልናል ፧ ይላሉ ።

4 ፤ የማይረባውን ፡ ቃል ፡ ይናገራሉ ፤ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ በሐሰት ፡ ይምላሉ ፤ ስለዚህ ፥ መርዛም ፡ ሣር ፡ በዕርሻ ፡ ትልም ፡ ላይ ፡ እንደሚበቅል ፥ መቅሠፍት ፡ ይበቅልባቸዋል ።

5 ፤ የሰማርያ ፡ ሰዎች ፡ ስለቤትአዌን ፡ እንቦሳ ፡ ይፈራሉ ፤ ክብሩም ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቷልና ፥ ሕዝቡ ፡ ያለቅሱለታል ፥ የጣዖቱ ፡ ካህናትም ፡ በሐዘን ፡ ይንተባተባሉ ።

6 ፤ ለንጉሡ ፡ ለኢያሪም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ይማረካል ፤ ኤፍሬምን ፡ ዕፍረት ፡ ይይዘዋል ፥ እስራኤልም ፡ በምክሩ ፡ ያፍራል ።

7 ፤ ሰማርያ ፡ ከንጉሧ ፡ ጋራ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ዐረፋ ፡ ጠፍታለች ።

8 ፤ የእስራኤል ፡ ኀጢአት ፡ የኾነው ፡ የአዌን ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ይፈርሳሉ ፤ ሾኽና ፡ አሜከላ ፡ በመሠዊያዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ይበቅላል ፤ ተራራዎችንም ፦ ክደኑን ፥ ኰረብታዎችንም ፦ ውደቁብን ፡ ይሏቸዋል ።

9 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ከጊብዓ ፡ ዘመን ፡ዠምረኽ ፡ ኀጢአትን ፡ ሠርተኻል ፤ በዚያ ፡ ጸንተዋል ፤ በጊብዓ ፡ ላይ ፡ ሰልፍ ፡ አይደርስባቸውምን ፧

10 ፤ በፈቀድኹም ፡ ጊዜ ፡ እገሥጻቸዋለኹ ፤ ስለ ፡ ኹለቱም ፡ ኀጢአታቸው ፡ በታሰሩ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ይሰበሰቡባቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

11 ፤ ኤፍሬም ፡ ማበራየት ፡ እንደ ፡ ለመደች ፡ ጊደር ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በዐንገቱ ፡ ውበት ፡ እጫንበታለኹ ፤ በኤፍሬም ፡
ላይ ፡ እጠምድበታለኹ ፥ ይሁዳም ፡ ያርሳል ፥ ያዕቆብም ፡ ዐፈሩን ፡ ያለሰልሳል ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፡ መጥቶ ፡ ጽድቅን ፡ እስኪያዘንብላችኹ ፡ ድረስ ፡ ርሱን ፡ የምትሹበት ፡ ዘመን ፡ ነውና ፥ ለእናንተ ፡
በጽድቅ ፡ ዝሩ ፥ እንደ ፡ ምሕረቱም ፡ መጠን ፡ ዕጨዱ ፥ ጥጋታችኹንም ፡ ዕረሱ ።

13 ፤ ክፋትን ፡ ዐርሳችኋል ፥ ኀጢአትንም ፡ ዐጭዳችኋል ፥ የሐሰትንም ፡ ፍሬ ፡ በልታችኋል ፤ በኀያላንኽ ፡
ብዛት ፥ በመንገድኽም ፡ ላይ ፡ ታምነኻልና ።

14 ፤ በሕዝብኽም ፡ መካከል ፡ ሽብር ፡ ይነሣል ፤ እናትም ፡ ከልጆቿ ፡ ጋራ ፡ በተፈጠፈጠች ፡ ጊዜ ፡ ሰልማን ፡
ቤትአርብኤልን ፡ በሰልፍ ፡ ቀን ፡ እንዳፈረሰ ፥ ዐምባዎችኽ ፡ ዅሉ ፡ ይፈርሳሉ ።

15 ፤ ከኀጢአታችኹም ፡ ክፋት ፡ የተነሣ ፡ ቤቴል ፡ እንዲሁ ፡ ያደርግባችኋል ፤ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ፈጽሞ ፡
ይጠፋል ።

____________________ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 11 ።

1 ፤ እስራኤል ፡ ሕፃን ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ወደድኹት ፥ ልጄንም ፡ ከግብጽ ፡ ጠራኹት ።

2 ፤ አብዝቼ ፡ ብጠራቸው ፡ አጥብቀው ፡ ከፊቴ ፡ ራቁ ፤ ለበዓሊምም ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ፥ ለተቀረጹ ፡ ምስሎችም ፡ ያጥኑ ፡
ነበር ።

3 ፤ እኔም ፡ ኤፍሬምን ፡ ክንዱን ፡ ይዤ ፡ በእግሩ ፡ እንዲኼድ ፡ መራኹት ፤ እኔም ፡ እፈውሳቸው ፡ እንደ ፡ ነበር ፡
አላወቁም ።

4 ፤ በሰው ፡ ገመድ ፡ በፍቅርም ፡ እስራት ፡ ሳብኋቸው ፤ ለእነርሱም ፡ ቀምበርን ፡ ከጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ እንደሚያነሣ ፡
ኾንኹ ፥ ድርቆሽም ፡ ጣልኹላቸው ።

5 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ አልወደዱምና ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ፥ አሶርም ፡ ንጉሣቸው ፡ ይኾናል ።

6 ፤ ከመከሩትም ፡ ምክር ፡ የተነሣ ፡ ሰይፍ ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ፥ ከበርቴዎችንም ፡ ያጠፋል ።

7 ፤ ሕዝቤም ፡ ከእኔ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ፤ ወደ ፡ ላይም ፡ ቢጠሯቸው ፡ ማንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡
አይችልም ።

8 ፤ ኤፍሬም ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ እጥልኻለኹ ፨ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እንዴትስ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥኻለኹ ፨ እንዴትስ ፡ እንደ ፡
አዳማ ፡ እጥልኻለኹ ፨ እንዴትስ ፡ እንደ ፡ ሲባዮ ፡ አደርግኻለኹ ፨ ልቤ ፡ በውስጤ ፡ ተናውጣለች ፥ ምሕረቴም ፡
ተነሣሥታለች ።

9 ፤ እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አይደለኹምና ፥ በመካከልኽም ፡ ቅዱሱ ፡ ነኝና ፡ የቍጣዬን ፡ መቅሠፍት ፡
አላደርግም ፥ ኤፍሬምንም ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልመለስም ፤ በመዓትም ፡ አልመጣም ።

10 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ይከተላሉ ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ያገሣል ፤ ባገሣም ፡ ጊዜ ፡ ልጆች ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡
ከምዕራብ ፡ ይመጣሉ ።

11 ፤ እንደ ፡ ወፍም ፡ ከግብጽ ፥ እንደ ፡ ርግብም ፡ ከአሶር ፡ ምድር ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ይመጣሉ ፤ በቤታቸውም ፡
አኖራቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

____________________ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 12 ።

1 ፤ ኤፍሬም ፡ በሐሰት ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ በተንኰል ፡ ከበበኝ ፤ ይሁዳም ፡ ከታመነው ፡ ቅዱሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ጋራ ፡ አይጸናም ።

2 ፤ ኤፍሬም ፡ ነፋስን ፡ ይበላል ፥ የምሥራቅንም ፡ ነፋስ ፡ ይከተላል ፤ ዅልጊዜም ፡ ሐሰትንና ፡ ተንኰልን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ያበዛል ፤ ከአሶር ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያደርጋሉ ፥ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳሉ ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ከይሁዳ ፡ ጋራ ፡ ክርክር ፡ አለው ፥ ያዕቆብንም ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ይቀጣል ፤ እንደ ፡
ሥራውም ፡ ይመልስለታል ።

4 ፤ በማሕፀን ፡ ውስጥ ፡ ወንድሙን ፡ በተረከዙ ፡ ያዘው ፥ በጕልማሳነቱም ፡ ጊዜ ፡ ከአምላክ ፡ ጋራ ፡ ታገለ ፤

5 ፤ ከመልአኩም ፡ ጋራ ፡ ታገሎ ፡ አሸነፈ ፤ አልቅሶም ፡ ለመነው ። በቤቴልም ፡ አገኘው ፥ በዚያም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡
ተነጋገረ ።

6 ፤ ርሱም ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ የመታሰቢያው ፡ ስም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

7 ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ተመለስ ፤ ምሕረትንና ፡ ፍርድን ፡ ጠብቅ ፥ ዘወትርም ፡ በአምላክኽ ፡ ታመን ።

8 ፤ ከከነዓን ፡ ወገን ፡ ነው ፤ በእጁ ፡ የተንኰል ፡ ሚዛን ፡ አለ ፥ ሽንገላንም ፡ ይወዳል ።

9 ፤ ኤፍሬምም ፦ ባለጠጋ ፡ ኾኛለኹ ፥ ሀብትንም ፡ አግኝቻለኹ ፥ በድካሜም ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአት ፡ የሚኾን ፡ በደል ፡
አይገኝብኝም ፡ አለ ።

10 ፤ እኔም ፡ ከግብጽ ፡ ዠምሬ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ እንደ ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በድንኳን ፡
እንድትኖር ፡ አደርግኻለኹ ።

11 ፤ ለነቢያትም ፡ ተናግሬያለኹ ፥ ራእይንም ፡ አብዝቻለኹ ፤ በነቢያትም ፡ እጅ ፡ ምሳሌዎችን ፡ አውጥቻለኹ ።

12 ፤ ኀጢአት ፡ በገለዓድ ፡ አለ ፤ ፈጽመው ፡ ከንቱ ፡ ናቸው ፤ ወይፈኖች ፡ በገልገላ ፡ ይሠዋሉ ፥ መሠዊያዎቻቸውም ፡
በዕርሻ ፡ ትልም ፡ ላይ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ይኾናሉ ።

13 ፤ ያዕቆብ ፡ ወደሶርያ ፡ አገር ፡ ሸሸ ፥ እስራኤልም ፡ ስለ ፡ ሚስት ፡ አገለገለ ፥ ስለ ፡ ሚስትም ፡ ጠባቂ ፡ ነበረ ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በነቢይ ፡ እጅ ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ አወጣ ፥ በነቢይም ፡ እጅ ፡ ጠበቀው ።

15 ፤ ኤፍሬም ፡ አስመርሮ ፡ አስቈጣው ፤ ስለዚህ ፥ ደሙ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ጌታውም ፡ ስድቡን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡
ይመልሳል ።

## ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ምዕራፍ ፡ 13 ።

1 ፤ ኤፍሬም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ፍርሀት ፡ ነበረ ፥ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ታበየ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዓልን ፡ በማምለክ ፡
በበደለ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ።

2 ፤ አኹንም ፡ ኀጢአትን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ጨመሩ ፤ በብራቸውም ፡ ለራሳቸው ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስልን ፥ እንደ ፡
ጥበባቸውም ፡ ጣዖታትን ፡ ሠርተዋል ፤ ኹሉም ፡ የሠራተኛ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ። ስለ ፡ እነርሱም ፦ የሚሠዉ ፡ ሰዎች ፡
እንቦሳውን ፡ ይሳሙ ፡ ይላሉ ።

3 ፤ ስለዚህም ፡ እንደ ፡ ማለዳ ፡ ደመና ፥ በጧትም ፡ እንደሚያልፍ ፡ ጠል ፥ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ከዐውድማ ፡
እንደሚበተን ፡ እብቅ ፥ ከመስኮትም ፡ እንደሚወጣ ፡ ጢስ ፡ ይኾናሉ ።

4 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ዠምሬ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡
አታውቅም ፥ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መድኀኒት ፡ የለም ።

5 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፥ እጅግ ፡ በደረቀ ፡ ምድር ፡ ዐውቄኽ ፡ ነበር ።

6 ፤ ከተሰማሩ ፡ በኋላ ፡ ጠገቡ ፥ በጠገቡም ፡ ጊዜ ፡ ልባቸው ፡ ታበየ ፤ ስለዚህ ፥ ረሱኝ ።

7 ፤ ስለዚህም ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ኾንኹባቸው ፥ እንደ ፡ ነብርም ፡ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ አደባባቸዋለኹ ፤

8 ፤ ልጇ ፡ እንደ ፡ ተነጠቀባት ፡ ድብ ፡ እገጥማቸዋለኹ ፥ የልባቸውንም ፡ ስብ ፡ እቀዳለኹ ፤ በዚያም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡
እበላቸዋለኹ ፥ የምድረ ፡ በዳም ፡ አውሬ ፡ ይነጣጠቃቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

9 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ በእኔ ፡ በረዳትኽ ፡ ላይ ፡ በመነሣትኽ ፡ ጥፋትኽ ፡ ነው ።

10 ፤ በየከተማኽ ፡ ኹሉ ፡ ያድንኽ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥኽ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ስለ ፡ እነርሱም ፦ ንጉሥንና ፡ አለቃዎችን ፡ ስጠኝ ፡ ብለኽ ፡ የተናገርኸው ፡ መሳፍንቶችኽ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

11 ፤ በቍጣዬ ፡ ንጉሥን ፡ ሰጠኹኽ ፥ በመዓቴም ፡ ሻርኹት ።

12 ፤ የኤፍሬም ፡ በደል ፡ ታስሯል ፥ ኀጢአቱም ፡ ተከማችቷል ።

13 ፤ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ጭንቅ ፡ ይመጣበታል ፤ በሚወለድበት ፡ ጊዜ ፡ በማሕፀን ፡ አፍ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ አይወጣምና ፡ አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ልጅ ፡ ነው ።

14 ፤ ከሲኦል ፡ እጅ ፡ እታደጋቸዋለኹ ፥ ከሞትም ፡ እቤዣቸዋለኹ ፤ ሞት ፡ ሆይ ፥ ቸነፈርኽ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ሲኦል ፡ ሆይ ፥ ማጥፋትኽ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ርኅራኄ ፡ ከዐይኔ ፡ ተሰወረች ።

15 ፤ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ፍሬያማ ፡ ቢኾን ፡ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ይመጣል ፥ የእግዚአብሔር ፡ ነፋስ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ይመጣል ፤ ምንጩንም ፡ ያደርቃል ፥ ፈሳሹንም ፡ ያጠፋል ፥ የተከበሩ ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ያሉበትን ፡ መዝገብ ፡ ይበዘብዛል ።

16 ፤ ሰማርያ ፡ በአምላኳ ፡ ላይ ፡ ዐምፃለችና ፡ በደሏን ፡ ትሸከማለች ፤ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፥ ሕፃኖቻቸውም ፡ ይፈጠፈጣሉ ፥ እርጉዞቻቸውም ፡ ይቀደዳሉ ።

## ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ምዕራፍ ፡ 14 ።

1 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ በኀጢአትኽ ፡ ወድቀኻልና ፥ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለስ ።

2 ፤ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ቃልን ፡ ውሰዱ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ተመልሳችኹ ፦ ኀጢአትን ፡ ኹሉ ፡ አስወግድ ፥ በቸርነትም ፡ ተቀበለን ፥ በወይፈንም ፡ ፋንታ ፡ የከንፈራችንን ፡ ፍሬ ፡ እንሰጣለን ።

3 ፤ አሶር ፡ አያድነንም ፤ በፈረስ ፡ ላይ ፡ አንቀመጥም ፤ ድኻ ፡ አደጉም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ምሕረትን ፡ ያገኛልና ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለእጆቻችን ፡ ሥራ ። አምላኮቻችን ፡ ናችኹ ፡ አንላቸውም ፡ በሉት ።

4 ፤ ቍጣዬ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመልሷልና ፥ ዐመፃቸውን ፡ እፈውሳለኹ ፥ በገዛ ፡ ፈቃዴ ፡ እወዳቸዋለኹ ።

5 ፤ ለእስራኤልም ፡ እንደ ፡ ጠል ፡ እኾነዋለኹ ፤ እንደ ፡ አበባም ፡ ያብባል ፥ እንደ ፡ ሊባኖስም ፡ ሥሩን ፡ ይሰዳል ።

6 ፤ ቅርንጫፎቹም ፡ ይዘረጋሉ ፥ ውበቱም ፡ እንደ ፡ ወይራ ፥ ሽታውም ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ይኾናል ።

7 ፤ ከጥላውም ፡ በታች ፡ የሚቀመጡ ፡ ይመለሳሉ ፤ ከእኽሉም ፡ የተነሣ ፡ ይጠግባሉ ፤ እንደ ፡ ወይንም ፡ ዐረግ ፡ ያብባሉ ፤ መታሰቢያውም ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይኾናል ።

8 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ጣዖት ፡ ለኤፍሬም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እኔ ፡ ሰምቼዋለኹ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ እመለከታለኹ ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ለመለመ ፡ ጥድ ፡ ነኝ ፤ ፍሬኽ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ።

9 ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ የሚያስተውል ፡ ጠቢብ ፥ የሚያውቃትም ፡ አስተዋይ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ቅን ፡ ነው ፥ ጻድቃንም ፡ ይኼዱበታል ፤ ተላላፊዎች ፡ ግን ፡ ይወድቁበታል ፨



www.ethiopianorthodox.org